# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 ፣የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን፤

www.ginbot7.org

ቁጥር 29 ሕዳር 25 2001 ዓ.ም


አንብበው
ያስነብቡ !
አባዝተው
ያሰራጩ !

> እንደሰው መኖራችንን የምናውቀው የዚህን አይነትን የጨለማ ሕይወት ለመግፈፍ በምናደርገው ትግል ነው !
>
> ዶ/ር ብርሀኑ ነጋ

## ወያኔ ያቋቋመው ቡድን ያቀረበውን ሪፖርት ግንቦት 7የፍትህ የነጻነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ አጣጣለው

የግንቦት 7 ንቅናቄ ሕዳር 19 ቀን 2001 ዓ.ም ባወጣው መግለጫ የመለስ አገዛዝ ታማኝ ወታደሮቹን በማዝመት በኦጋዴን ክልል ሰላማዊ ዜጎች ላይ ከፍተኛ የሆነ የሰብ ዓዊ መብት ጥሰት መፈፀሙን አስታውሶ የዜጎችን መኖሪያ መንደርን ማቃጠል፣ እናቶችና ወጣት ሴቶችን አስገድዶ መድፈር፣ ህጻናትና ሽማግሌዎች ሳይቀሩ በእስርና ግርፋት ማሰቃየት በጠራራ ጸሃይ በግፍ ከተፈጸመው የጅምላ ጭፍጨፋ ጋር ተዳምሮ የመለስ ዜናዊን አገዛዝ በዘር ማጥፋት ወንጀል ተጠያቂ ሊያደርግ እንደሚገባ ከጭፍጨፋው ተርፈው በተለያዩ የእርዳታ ጣቢያዎች የሚገኙ የአይን እማኞችን ዋብ አዲርገውና ከሳታላይት በተነሳ የምስል መስረጃ አስደግፈው የተለያዩ አለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ተሟጋች ድርጅቶች ለአለም አቀፉ ህብረተሰብ አቤቱታ እያቀረቡ መሆኑ ተገቢ እርምጃ ነው ብሎ እንድሚያምን አረጋግጦአል ። **(ወደ ገጽ 4 ዞሯል)**

## የረሀብ ድረሱልኝ ድምጽ ከትግራይ

ኢሪን ህዳር18 ቀን 2001ዓ.ም ባወጣው ዘገባ በትግራይ ካሉት ሰላሳ አራት ወረዳዎች ሃያ ሰባቱ ወረዳዎች አስቸኳይ የምግብ እርዳታ እንደሚያስፍልጋቸው ጥያቄ መቅረቡን ዘግቧል።በትግራይ ምስራቃዊ ዞን ያሉት ክልተ አውላሎ፣አስቢ ወንበርታ እና ጸጸዳ አምባት ነዋሪዎች፣ ነፍሳቸውን ለማትረፍ ወደ ተቀሩት የሀገሪቱ ክፍሎች እንደሚሰደዱ ለኢሪን ገልጸዋል።እነዚህ አርሶ አደሮች ነፍሳቸውን ለማትረፍ ወደ ተለያዩ የኢትዮድያ ክፍሎች እንደሚሰደዱ መጠቆማቸው አንድም ከወያኔ ምንም እርዳታ በበእንደማይጠብቁ እና አገዛዙ ላይ አንዳች እምነት እንደሌላቸው በግልጽ የሚያሳይ ሲሆን በሌላ በኩል አገዛዙ የትግራይ ህዝብ የተቀሩት ወገኖቹን እንዲፈራና እንደጭራቅ እንዲመለከት ለዘመናት ካለማቋረጥ ለነዛው ፕሮፓጋንዳ ማንም ቁብ እንዳልሰጠው የሚያሳይ መሆኑን ታዛቢዎች ተናግረዋል።

የኢሪን ዘጋቢ ያናገራቸው አንዳንድ አርሶአደሮች እንደገለጹት የቀሯቸው ንብረቶች ጥቂት ከብቶች ብቻ መሆናቸውን ጠቅሰው፣ ምንም እንኳን የከብቶች ዋጋ ቢያሽቆለቁልም ከብቶቻቸውን ሸጠው የቤተሰባቸውን ህይወት ለማትረፍ እንደሚያስቡ ገልጸዋል።

አቶ ገብረ መድህን ገብረጊዮስ የተባሉ አርሶ አደር “ለመኖር የተወሰኑ ከብቶች መሸጥ አለብኝ ፣ነገር ግን ከብቶች የሚገዛ በገበያው የለም” ሲሉ ጭንቀታቸውን …

**(ወደ ገጽ 2 ዞሯል)**

## ...የሰራልሽ ቀርቶ የገደለሽ በላ! ፍርደ ገምድል ውሳኔ በንጹሁ ቴዲ!

በትናንቱ እለት ታዋቂውና ተወዳጁ ድምጻዊ ቴዎድሮስ ካሳሁን (ቴዲ አፍሮ) ለ8 ወር 19 ቀናት በእስራት ሲንገላታበት የከረመው ክስ በከፍተኛው ፍርድቡት በስምንተኛው ችሎት የመለስ ዜናዊን ዘረኛ ፍላጎት ለማስፈጸም በተሰየሙ ዳኖች አመካይነት ቴዲን ወንጀለኛ በማድርግ መወሰኑ ቡዙዎቹን ያሳዘነ ሆኗል። ፍርድ ቤት ተብዬው የቅጣት ውሳኔ ለመስጠት ሌላ ቀጠሮ የያዘ መሆኑም ከአዲስ አበብ ዘጋቢያችን አስታውቋል።

**(ወደ ገጽ 4 ዞሯል)**

## ወያኔ ልመናውን በውጭ አገር አስፋፍቶ ቀጥሏል

በትናንት እለት በተለያዩ ሃገራት ኤምባሲዎች ውስጥ የተጀመረው፣ በአለምአቀፍ ድርጅቶች ውስጥ የሚሰሩትን ኢትዮጵያውያንን ለስብሰባ በመጥራት ገንዘብ ለድህነትና ረሃብን ለማጥፊያ አዋጡ የሚለው የወያኔ ጥያቄ ዱብ እዳ የሆነባቸው እነዚሁ ኢትዮጵያውን ለግንቦት ሰባት እንደገለጹት ይህ የገንዘብ ጥያቄ ከአገዛዙ ማእከል የታቀደ ለመሆኑ ማስረጃው አገዛዙ ከኢትዮጵያ አዘጋጅቶ የላከው ባለ አምስት ዶላር ቲኬት በስብሰባው ላይ መቅረቡ ነው፡፡ ተስብሳቢዎቹ የተጠየቁት በወር አንድ ግዜ የአምስት ዶላር ቲኬት እንዲገዙ መሆኑን የተረዱት ተሰብሳዎች አገዛዙ የሃገሪቱን የውጭ ምንዛሪ በገፍ እያጋዘ በአስመጭና ላኪ የንግድ ኩባንያዎቹ ወደ ውጭ ከሚልከው በርካታ ሸቀጥ ሚያገኘውን ውጭ ምነዛሪ በውች ሃገሮች ባንክ እያካበተ ለምን ከእነሱ 5 ዶላር ለመጠየቅ እንዳሰበ ያስገረማቸው መሆኑን አልደበቁም፡፡ እንዲህ አይነቱ ስብሰባ ከተደረገባቸው ቦታዎች አንዱ ካርቱም የሚገኘው ኤምባሲ ሲሆን ስብሰባውን የመራው እነ መለስ ዜናዊ ለአስራ ሰባት አመት እንዳሻቸው በሚጋለቡት የአገዛዙ አምባሳደር በአሊ አብዶ ነበር፡፡

ይህ አምስት ዶላር አዋጡ በሚል ሰበብ የተጀመረ ስብሳባ ከጀርባው ምን ይዞ ሊሆን ይችላል የሚል ጥርጣሬ ያደረባቸው ተሰብሳቢዎች፣ ወያኔ ከአምስተ ብር ተነስቶ እየዋላና እደረ ገንዘብ ከፍ ያለ ገንዝበ አምጡ ለማለት ሁኔውን የሚፈትንበት ወይም ከእዚህ የገንዝብ ማሰባሰብ ስም በመፈጠረው አጋጣሚ በአለም አቀፍ ድርጅቶች ውስጥ ከሚሰሩ መሃል ስርአቱን የሚያገለግል የዲፕሎማሲ ስራ የሚሰሩለትን ለመመልመል ያሰበበት ሊሆን ይችላል የሚል ጥርጣሬ አሳድሯል፡፡

ይህ ገንዝብ የማሰባሰብ እቅድ በአለም አቀፍ ድርጅቶች ውስጥ ከሚሰራው ኢትዮጵያዊ አልፎ ሌላውንም በውጭ ሃገር ወያኔ ሊሰባስበው የሚችለውን ዜጋ የሚጨምር መሆኑ ወደፊት የሚታይ መሆኑን የገለጹት ለተመሳሳይ ስብሳባ ተጋብዘው የነበሩ ኢትዮጵያዊ እንደሚሉት “ወያኔ በህዝብ አመኔታ ካጣ በኋላ፣ የህዘብና የሃገር ጥቅም የሚባል ነገር የማያስብ ነው በማለት ሃገሬው እርሙን ካወጣ በኋላ፣ ድህነትና ረሃብና በሃገር ለሚያስፋፋ አገዛዝ ደህነትና ረሃብን ቀንሱበት ብሎ ገንዘብ የሚለግሰው በአለምአቀፍ ተቋማት ውስጥ የሚሰራ ሆነ በውጭ ሃገር የሚኖር ብዙ ኢትዮጵያዊ አይገኝም፡፡ ወያኔ በተለያዩ ጥቅማ ጥቅሞች ከገዛቸው ወይም በሃገር ቤት ባላቸው ንብረትና ሃብት ላይ ጉዳት ሊያደርስብን ይችላል ከሚል ፍረቻ ተገደው ገንዘብ ሊያዋጡለት ከሚችሉ ጥቂት ግለሰቦች በስተቀር ሌላው ኢተዮጵያዊ ዜጋ ገንዘቡን አዋጥቶ ለወያኔ ሲያስረከብ ፈጽሞ አይታየኝም›” ብለዋል፡፡ **(ወደ ገጽ 2 ዞሯል)**

## የአየር ሞገድ ማስታወቂያ

**ግንቦት7 የፍትህ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ በሳምንት 3 ቀናት ማለትም ማክሰኞ ፣ ሃሙስ ና ቅዳሜ እንደ ኢትዮጵያ ሰዓት አቆጣጠር ከምሽቱ 2 ሰዓት አስከ 2 ሰዓት ተኩል ወደ ኢትዮጵያና ሌሎች የአለማችን ክፍሎች በአማርኛ ቋንቋ የሚያስተላልፈውን የሬዲዮ ፕሮግራም በ12120 ኪሎኸርዝ፣ አጭር ሞገድ በ25 ሜትር ባንድ እና በ11530 ኪሎኸርዝ በተመሳሳይ ሜትር ባንድ ላይ የሚያሰራጭ መሆኑን ይገልጻል፡፡**

**የመለስ ዜናዊ የአፈና ቡድን ስርጭታችን በአገር ውስጥ እንዳይሰማ በቅርቡ ከቻይና ባስገባው መሳሪያ እያስተጓጎለ ስለሆነ ችግሩን ለመቋቋም የሚያስችል አቅም እንድናጎለብት ስርጭታችን መሰማት አለመሰማቱን ለዝግጅት ክፍላችን በሚከተለው የኢሜልና ስልክ አድራሻ እንድታሳውቁን ወገናዊ ጥሪያችንን እናቀርባለን፡፡**


Email info@ginbot7.org, PR@ginbot7.org, foreign@ginbot7.org, Org@ginbot7.org, or political@ginbot7.org Tel- +44 208 133 5670

# ርእሰ አንቀጽ



## ሁላችንም ተጠያቂዎች ነን፡፡ ማስተሰሪያችን የድርሻችንን ማበርከት ብቻ ነው፡፡

በሃገራችን ላይ ለሚፈጸመው ክህደት፣ ለሚታየው የሰብአዊ መብት ረገጣ፣ ለሰፈነው የፍትህ ፍንገጣ፣ ለአብዛኛው ህዝብ ከጎዳና አደር ውሻ ያልተሻለ ህይወት፣ ዘረኛ ለሆኑ ጥቂት ጸረ- ኢትዮጵያ ሃይሎች የእብሪት እብጠት፣ ሚሊዮኖች ለምንገኝበት አሳፋሪ ውርደት፣ ማነው ተጠያቂው በማለት ግንቦት 7 ጠይቆ በማያሻማ ቋንቋ ምላሹን አስቀምጧል፡፡ በእዚህ ምላሹ ግንቦት 7 ስልጣን ላይ ያለውን አምባገነናዊና ዘረኛ አገዛዝ ብቻ ተጠያቂ አላደረገም፡፡ በሃገራችንና በራሳችን ላይ ለተከመረው አበሳና ለደረሰው መከራ እኛም ተጠያቂዎች መሆናችን እንድናውቅ የትውልዳችንን ፈተና ከህሊናችን ደጃፍ አምጥቶ ከምሮታል፡፡

የትግሉን ቀጠና ዘረኞችና ጸረ-ኢትዮጵያ የሆኑ ሃይሎች ያለ የሌለ ሃይላቸውንና ጥሪታቸውንና እውቀታቸውን አሰባስበው ለኢትየጵያችን ውድመት ለብቻቸው እንዲፈነጩበት ትቶ ዝምታን፣ አንገት ደፍቶ መኖርን ወይም ስደትን የመረጠው በመሉ እንደ እውቀቱና ሃብቱ ብዛት እንደ ጉልበቱ ጥንካሬ ተጠያቂ ነው ብለናል፡፡ ገዥዎቻችን በሃገራችንና በሁላችንም ላይ የሚፈጽሙት በደልና ግፍ እኛ በፈቀድልናቸው መጠን መሆኑን መገንዘብ የሃገራችንን ህልውና ለማጥበቅ፣ መብት የተከበረባት፣ ሰለምና መረጋገት የሰፈነባት ብልጽግና የተላበሰች ኢትዮጵያን ለማየት የሚያስችለን የመጀመሪው ታላቅ እርምጃ ነው ብሏል፤ ግንቦት 7፡፡

ይህ ግንዛቤ በቅድሚያ ራሳችንን ሰብአዊ ፍጥረቶች፣ ቀጥሎም የአንድ ሃገር ዜጋ አድርገን ማየት የምንችልበት የማንነታችን የመሰረት ድንጊያ ነው፡፡ ሰው ሆነን በሌላ ሰው የተጫነብንን የባርነት ቀንበር ተቀብለን ለመኖር ከወሰንን ሰው ከሚባለው ምድብ እራሳችንን ማውጣት ይኖርብናል፡፡ ማህበረ-ሰብእ የቆመበትን መሰረታዊ የፍትህ መርህ የሚንድ፣ የእንዳንዱ ዜጋ መበት፣ ንብረትና ህይወት ለመንከባከብ መቆም የሚገባው መንግስታዊ ስርአት በአውሬዎች ተይዞ፣ ህገ-አራዊትን ማደሪያው ሲያደርግ ዝም ብለን ከፈቀድን፣ እራሳችንን የአንድ ሃገር ዜጋ፣ የአንድ ማህበረ-ሰብእ አባል አድርገን ከምናይበት ተርታ ማውጣት ይኖርብናል፡፡

ዛሬ እንደህዝብና እንደሃገር የደረስንበት አሳሳቢና አሳዛኝ የታሪክ ምእራፍ እስከዛሬ ሁላችንም እያወቅን በመገባበዝ ብቻ ሁላችንም አፍነነው የኖርነው አሳፋሪ የማንነታችንን ገጽታ ፣ በሚያንገሸግሹ ቃለት መደበቂያ አስክናጣ ድረስ ሊነገረን እንደሚያስፈልግ የግድ ብሏል፡፡ ውብና የሚያምረውን ታረካችንን፣ ቀደምቶቻችን ለነጻነታቸው የፈጸሙትን ገድልና የከፈሉትን መስዋእትነት፣ ገንብተውት የነበረውን ገናና ስልጣኔ፣ በየድርሰቱ በየግጥሙ በየዲስኩሩ እየሰነቀርን፣ በጥልፍ ስራው፣ በስእሉና በቅርጻ ቅርጹ ላይ እየለጠፍን፣ በየድግሱና በየሰርጉ እያውለበለብን፣ የሚከረፈውን የስቃይ፣ የመከራና ውርደት ኑሯችንን የሚያስረሳ አደንዛዥ እጽ እንዳደረግነው ሊነገረን ይገባል፡፡ ኢትዮጵያ የምንላት ሃገርና ህዝቧ ያሉበትን ሁኔታ ከምር ተመልክተን፣ የቀደምቶቻችን ታሪክ ወራሽነት፣ የእዛች ሃገር ዜግነት፣ የአረንጓዴ፣ ቢጫና ቀይ ባንዲራችን ለባሽነት ይገባናል ለማለት ድፍረቱ የሚኖረን ስንቶቻችን እንሆን? ይህንን የኢትዮጵዊነት ክብር በተግባራችን ያገኘነው ሽልማት ሳይሆን በመወለዳችን ያካሄድነው ዘረፋ ነው ቢባል ይበዛ ይሆን? አይመስለንም፡፡

ቀደምቶቻችንን ለነጻነታቸው ቀናኢ ነበሩ፡፡ ለሀገራቸው ህልውና ሲሉ የማይከፍሉት መስወአትነት አልነበረም፡፡ ጥቃትና በደለን የሚያስመርጥ፣ እንዲሁ በበድናቸው የሚያንከላወስ የመኖር ብቻ ሱስ አልነበራቸውም፡፡ ሃገራቸው አደጋ ላይ ስትወድቅ በጋራ ለመመከት፣ የማይገድሉት የግል ጥላቻና ቂም፣ የማይቀብሩት የግል ጥቅምና ፍለጎት፣ ይቅርታ የማያደርጉለት የግል በዳይና ባላንጣ አልነበረም፡፡

ቀደምቶቻችን በተናጠል ተንጠልጥሎ የሚከበር የማህበረ-ሰብእ ነጻነት፣ የሃገር ህልውና እንደሌለ ያውቁ ነበርና ፈተናው በበዛ ቁጥር አንድነታቸውን አጥብቀው ለመስዋእትነት ተሽቀዳድመው ያቆዩትን ሃገር ጥለን ነው፤ ዛሬ እኛ በምርጫችን፤ አዎን በምርጫችን አንገታችንን ደፍተን በባርነት ወይም ሃገራችንን ለጸረ-ኢትዮጵያ ሃይሎች አስረክበን በስደት ለመኖር የመረጥነው፡፡ "ከእንዲህ አይነቱ ወቀሳ ለመዳን፣ እንዴት እንዲህ ተባልን? ይህን የሚለን ምን አይነቱ ደፋር ነው?" ሊባል ይቻላል፡፡ እውነታውን ግን መቀየር አይቻለንም፡፡

"በጋራ ለመነሳትና ለመታግል ዛሬም እንደጥንቱ መሪ፣ አሰባሳቢና አስተባበሪ ያስፈልጋል" እንደሚባል እናውቃለን፡፡ ከእዚህም ጋር ተያያዞ "የሚመጥነን መሪ አሰባሰቢና ድርጅት አላገኘንም፡፡ እኛ ለመታገል ያቅማችንን ለማድረግ አልቦዘንም" እንደሚባል ይገባናል፡፡ ይህ ግን ወንዝ የማያሻገር ምክንያት ነው፡፡ ልክ ገዥዎቻችን በሃገራችን ላይ ለሚያደርሱት ጥፋት እኛም በድርሻችን ተጠያቂዎች ነን እንዳልነው፣ የፖለቲካ ድርጅቶችና መሪዎች ለሚያጠፉትም ጥፋት የራሳችንን የተጠያቂነት ድርሻ መቀብል ይኖርብናል፡፡ የድርጅት መሪዎች፣ የሰጠናቸውን አደራ አመኔታ የሚበሉት፣ በራሰችን ድጋፍ ላይ ተነስተው በአናታችን ላይ እንሽና የሚሉት እኛው አስከፈቀድልናቸው ድረስ ብቻ መሆኑን ማወቅ አለብን፡፡ ሲያጠፉ ለማረም፣ ሲያባክኑ ለመጠየቅ፣ ሲጠግቡ ለማስወገድ የሞራልና የሰብአዊ ግዴታ የማይሰማው ዜጋ ዞሮ ዞሮ ከተመክሮ ለመማር ባለመፍቀዱ በሚሰጠው ጭፍን ድጋፍና አመኔታ፣ በድርጅቶችና በመሪዎቻቸው በሚቀሰቀስ የከህድት አዙሪት ደግሞ ደጋሞ መደፈቁ አይቀርም፡፡ የሃገርን ህልውናና የራስን ህይወት በሚያክሉ ታላላቅ ቁም ነገሮች ላይ ግዙፍ በደል የሚፈጽሙበትን በይሉኝታና በጭፍን ተከታይነት ተሸክሞ ለመቀጠል ወይም ሳይጠይቅ ለማለፍ የሚሻ ዜጋ በድርጅቶችና በመሪዎች ላይ የጅምላ ክሱንና ምሬቱን የመደርደር መብት የለውም፡፡ ከእዚህ የድርጅቶች የጅምላ ውግዘት ተነስቶ፣ ድርጀቶችንና መሪዎቻቸውን በመኮነን የራስን የመስወአትነት ድርሻ ላለመክፈል የሚያደረገው ጥረት ተቀባይነት የሌለው ነው የምንለው፡፡

የኢትዮጵችን ጉዳይ፣ የነጻነታችንና የመብታችን ጉዳይ የገዢዎቻችንን እብሪትና ጭካኔ ፈርተን የማንተወው ከሆነ፤ በተመሳሳዩም፣ በተለያዩ ወቅቶች የሃገርና የወገንን ጉዳይ በሚመለከት ሃላፊነትና አመኔታችንን ሰጥተናቸው በከዱን መሪዎችና ድርጅቶች የተነሳ የማንተው መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ በእዚህ ከተስማማን የሚቀረን አማራጭ አንድ ብቻ ነው፡፡ ከወደቅንበት መነሳት፣ ቅሌን ጨርቄንና የእናቴ መቀነት የሚል ሰበብ ሳንሰጥ፣ ኢትዮጵያዊ ሊያሰኘን የሚገባውን ተግባር ለመፈጸም መሰባሰብና የድረሻችንን ማበርከት ብቻ ነው፡፡ ለሊቱ የሚነጋው፣ እንደ ሃገርና እንደ ህዝብ ትንሳኤያችን እውን የሚሆነው፣ በግለሰብ፣ በቤተሰብና በትውልድ ደረጃ የምናስተሰርየው፤ ይብቃ ዘረኛነት! ይብቃ አድሎ! ይብቃ ክህደት! ይብቃ ባርነት! ይብቃ ድህነት! ይብቃ በሽታ! ይብቃ መሃይምነት ይብቃ ጥላቻ! ይብቃ ፍትህ መ ፈንገጥ! ብለን በአንድነት አምረን በዘረኞች፣ በአምባገነኖችና በዘራፊዎች ላይ ለመነሳት ስንቆርጥ ብቻ ነው፡፡

## የረሀብ ድረሱልኝ... (ከገጽ 1 የዞረ)

ጠቁመዋል።የስምንት ልጆች አባት የሆኑት አቶ ገብረ መድህን ስምንተኛ ክፍል የደረሰ ልጅ ቢኖራቸውም ወደ ሁለተኛ ደረጃለመላክ አቅም እንደሌላቸው እና የቤተሰባቸውን ህልውና ለማቆየት ቅድሚያ እንደሚሰጡ ተናግረዋል።

የአስራ ሰባት አመቷ የውቅሮ ነዋሪ ብርዛፍ ጺጋዬ በበኩሏ ቤተሰቧ በቅርቡ ያመረተው እህል በጣም ጥቂት እና ለአንድ ወር ቀለብነት እንኳን እንደማይበቃ ተናግራለች።ብርዛፍ ደብተር መግዛት አቅቷት ከሶስተኛ ክፍል ትምህርቷን ማቋረጧን ፣እህቷም እንደሷ ትምህርቷን ለማቋረጥ መገደዷን ገልፃለች።

እንደ አቶ ገብረመድህን አይነት የተራቡ ልጆች በሚበዙባት ትግራይ፣ በቅርቡ ወያኔ አንድ ሺህ ሶስት መቶ የሚደርሱ ትምህርት ቤቶችን አሰራለሁ ብሎ ገንዘብ መሰብሰቡ፣አገዛዙ ፍጽም ሀፈረተ ቢስ እና እወክለዋለሁ ለሚለው ህዝብ ያለውን ንቀት የሚገልጽ ከመሆኑም ባሻገር የትግራይ ህዝብ ከሌላው የበለጠ ተጠቃሚ እንደሆነ አርድጎ ለማሳየት የተደረገ መሰሪ ሙከራ ነው ይላሉ ፤ታዛቢዎች።እነዚህ ታዛቢዎች "ለመሆኑ የተራበ ህፃን እንዴት ብሎ ትምህርት ቤት ሊሄድ ይቻለዋል?" ሲ ሉ ይጠይቃሉ።

እነ መለስ ዜናዊ ልጆቻቸውን በአሜሪካ እና በእንግሊዝ በሚገኙ ውድ ዩኒቨርስቲዎች በአመት እስከ ሃምሳ ሺህ የአሜሪካ ዶላር እየከፈሉ እንደሚያስተምሩና በትግራይ ህዝብ ስም እነመለስ ዜናዊ የሚነግዱበት የፋብሪካ፣ የትራነስፖርት፣ የኮነስትራክሽን፣ የባንክና የኢንሹራነስ የንግድ ኢምፓየር ጥቂቶች የወያኔ ባለስልጣናትንና ከእነዚህ የተጠጉ ግለሰቦችን የናጠጠ እንደሆነ የሚታወቅ ሲሆን፤ እነዚህ ኩባንያዎች በሚካሄድባቸው ዘረፋ የተነሳ ከባንክ በመለስ ዜናዊ ትእዛዝ የወሰዱትን በቢሊዮን የሚቆጠር ብር ዋናውን መመለስ ቀርቶ ወለዱን እንኳን አንደማይከፍሉ ከባንክ የግንቦት 7 ድምጽ መዘገቡ ይታወሳል፡፡

## ወያኔ ልመናውን.... (ከገጽ 1 የቀጠለ)

ሌላው ተሰብሳቢ እንዳሉት "ከዚህ በፊትም ወያኔ በሀገሪቱ ላይ በተለያየ ጊዜ የደረሱትን ሰው ሰራሽ እና የተፈጥሮ ችግሮችን ምክንያት በማድረግ በተለያዩ ጊዜያት በእርዳታ ስም ሲያሰባስብ የቆየውን ገንዘብ ለተጎጂዎች ሳያደርስ መቅረቱ፤ እንዲሁም ከውጭ የእርዳታ ድርጅቶች የተገኙ የምግብና የገንዘብ እርዳታዎች ለቱባ የወያኔ ባለስልጣናት ኪስ ማደለቢያ የፖለቲካ ታማኝትን መግዣ የፖለቲካ ተቃዋሚን ማጥቂያ መሳሪያ ሆነው መቅረታቸውን አገሬው በሙሉ ስለሚያውቅ እውነት በእዚህ መንገድ ገንዘብ ሰብስቤ የውጭ ምንዛሪ ችግሬን እወጣለሁ ብሎ መለስ ዜናዊ አስቦ ከሆነ እውነትም እእምሮውን ስቷል ለማለት እደፍራለሁ" ብለዋል፡፡

አያይዘውም ‹‹ገንዘብ ከማሰባሰቡም በላይ ከጀርባው በውጭ የሚገኙ ኢትዮጵያውያንን እንደዚህ ቀደሙ ሁሉ በየኤምባሲው በመጥራት እና በኢትዮጵያ ሰላም መስፈኑን በመስበክ ወደ አገር ቤት እንዲገቡ ለማነሳሳት፤ በዚህም ለአለም ህብረተሰብ በኢትየጵያ ውስጥ ሰላም እንደሰፈነ፣ መብት እንደተከበረ፣ መልካም አስተዳደር እንዳለ በማስመሰል በረሀብ፣ በእስራትና በግድያ እየተሰቃየ ያለውን ህዝብ ጩኸት ለማፈንና ሀገሪቱን በማን አለብኝነት ለመዝረፍ ወያኔ የዘረጋው መርህ ግብር ሊሆን ይችላል፡፡ በውጭ የሚገኘው ኢትዮጵያዊን ለዚህ አገርን የማጥፋት ዘመቻ ተባባሪ እንደማይሆን ተስፋ አለኝ ብለዋል፡፡

ግንቦት 7 ድምጽ በግንቦት 7 ለፍትህ ለነጻነትና ለዴሞክራሲ ንቅናቄ የህዝብ ግንኙነትና ቅስቀሳ ዘርፍ በሳምንት አንዴ የሚዘጋጅ ድርጅታዊ ልሳን

የፖስታ ሳጥን ቁጥር :- POBox: 4916
2003EX Haarlem
The Netherlands

## ሃይለ ሀሳብ

# ከዶ/ር ብርሀኑ ነጋ ጋር የተደረገ ቃለ ምልልስ ክፍል ሁለት)

**ዶ/ር ብርሃኑ** በዚህ መንግስት መውደቅ ላይ ስምምነት ከኖረ በሁዋላ የሚነሳው ሁለተኛው ጥያቄ እንዴት ነው የሚወድቀው የሚለው ነው፡፡ በተለይም በአመፅ ሊወድቅ ይችላል ወይ? ዋጋውስ ከፍተኛ አይሆንም ወይ; የሚለው ነው፡፡ ይህ ጥያቄ ከበፊተኛው ጥያቄ ጋር ተዛምዶ መመለስ ይኖርበታል፡፡ በመጀመሪያ ምንም በማያጣላው ጉዳይ ላይ ግልፅ እንሁን፡፡ ይህ መንግስት ከአመፅ ውጭ፣ በተለይም ደግሞ በሰላማዊ መንገድ መውደቅ ቢችል የሚጠላ፣ በተለይ በኛ ድርጅት አባላት መሀከል እንደሌለ አውቃለሁ፡፡ ብዙዎቻችን የሰላማዊ ትግልን ተመራጭነት ስንሰብክ የነበርን ነን፡፡ ይህን አገዛዝ በሰላም ተገላግለን፡ ሁላችንም ይህ ማለቂያ የሌለው የሚመስለው የኢትዮጵያ የትርምስ ፖለቲካ ቀርቶ ሊመሩን የሚፈልጉትን በተወሰነ ጊዜ እየመረጥን ሌላ ጊዜያችንን ሁላችንም እንደሙያችንና እንደፍላጎታችን አገራችንን ብናገለግል ወይም ደግሞ ዝም ብለን ልጆቻችንን እያሳደግን በሰላም ብንኖር በጣም የምንመርጥ ነን፡፡ ለኛ ጥያቄው የትኛው የትግል ስልት ይሻላል የሚለው የተሳሳተ ጥያቄ ሳይሆን፣ ከዚህ በፊት በሞከርነው መንገድ እንደማይወድቅ እርግጠኛ እስከሆንን ድረስ (ይህንን ለምን እንደሆነ ቀደም ብዬ ጠቅሼዋለሁ) ዝም ብለን አንገታችንን ደፍተን፣ በራሱ ሀይል ደክሞት እስከሚወድቅ ድረስ እንገዛ ወይንስ ባለን አቅም ታግለነው የመከራ ጊዜያችንን እናሳጥር? የሚለው ነው፡፡ ለዚህም በደንብ አስበንበት፣ አውጥተን አውርደን፣ ለኛ የማያዳግም የምንለው መደምደሚያ ላይ ደርሰናል፡፡

በመጀመሪያ ይህ መንግስት አንዳንዶች እንደሚያስቡት በጉልበትም ቢሆን ጠንካራ ነው ብለን አናምንም፡፡ ጉልበቱ እንደፈሪ በደካሞች ላይ፣ ምንም ባልታጠቁ ሰላማዊ ሰዎች ላይ እንጂ፣ በሶማልያም በኦጋዴንም በሌሎችም ራሳቸውን ለመከላከል ከቆረጡ ሀይሎች ጋር በሚደረግ ግጥሚያ እንዳየነው ልዩ የሚያሰኝ ምንም ሀይል እንደሌለው ከልባችን እናምናለን፡፡ በተለይ ይህ ብዥታ ጠርቶ ኢትዮጵያውያንን በያሉበት እራሳቸውን ሊከላከሉ በሚችሉበት መንገድ ማደራጀት ከተቻለና ወጥ የሆነ፣ በእውቀትና በሙያ ላይ የተመሰረተ አመራር መስጠት ከተቻለ (ይህ ደግሞ ይቻላል ብለን እናምናለን) በጣም ከባድ፣ ማለቂያ የሌለው ረጅም ጊዜ የሚፈጅ ግጥሚያ ይሆናል ብለን አናምንም፡፡ ይህም የሚታይበት ጊዜ ሩቅ ይሆናል የሚል እምነት የለንም፡፡ ከዚያ ይልቅ ግን ለእምነታችን መሰረት የሆነው አመለካከታችን ሰው ስለመሆናችን ያለን አመለካከት ነው፡፡ በደልን፣ ጭቆናን፣ ግፍን፣ ውርደትን፣ ለከት የሌለው ትእቢትን፣ ፍፁም ሁዋላ ቀር የሆነ ዘረኛነትን ዝም ብሎ መቀበል የእግዚአብሄር ስጦታ የሆነውን ሰውነታችንን እርግፍ አድርገን ጥለን ከእንሰሳት ተርታ መቀላቀልን መምረጥ ሆኖ ስለሚሰማን ነው፡፡ ለኛ ሕይወት ዝም ብሎ ቀን መቁጠር ነው ብለን አናምንም፡፡ መኖራችንን የምናውቀው እንዲህ አይነቱን በደል ላለመቀበል በየቀኑ በምናደርገው ትግል ነው፡፡ ስለዚህ የትግላችንን ውጤት በአጭር ጊዜ የማናገኘው ነው ብለን እንኳዋን ብናምን፣ እንደሰው መኖራችንን የምናውቀው የዚህን አይነትን የጨለማ ሕይወት ለመግፈፍ በምናደርገው ትግል ነው ነው የምንለው፡፡

ስለዚህ ይህን የትግል መንገድ ስንመርጥ ቀላል ይሆናል፣ ብዙ ችግር አይገጥመንም፣ ከሚል ተስፈኛ ስሜት በመነሳት ሳይሆን፣ ከመታገል በቀር ምንም አማራጭ የለንም ብለን ስለደመደምን ነው፡፡ ዝም ብሎ ግፍን ተቀብሎ መቀመጥን እንደ ኑሮ ስለማንቆጥረው ነው፡፡ ይህ ብቻ አይደለም፡፡ በእንዲህ አይነት የውርደት ኑሮ የሚያልፈው እያንዳንዱ ቀን ከሕይወታችን ተመንጭቆ የተወሰደ ብርቅ ጊዜ አድርገን ስለምንወስደው ነው ምንም ገደብ የሌለው ትእግስት የሌለን፡፡ በራሱ ጊዜ እስከሚወድቅ ለአስርም፣ ለሀያም፣ ከዚያም በላይ ለሆኑ አመታት ዝም ብለን እንጠብቅ የሚል አመለካከት በፍፁም የማይዋጥልንም ለዚህ ነው፡፡ ይህ ብቻ አይደለም፡፡ ለእኛ አገራችን እንደ አገር ለመኖር እንደዚህ አይነት ረጅም ጊዜ በነኝህ ሰዎች እጅ መቆየት አትችልም ብለን ከልባችን ስለምናምንም ነው የነኝህን ሰዎች አገዛዝ በሁሉም መንገድ ተረባርበን ማሳጠር አለብን የምንለው፡፡ ይህ ጊዜ ደግሞ አጭር እንደሚሆን ቅንጣት ታክል ጥርጥር የለንም፡፡

ሌላው ከዚህ ጋር የሚነሳው ጥያቄ በዚህ መልክ በአመፅ የሚመጣው ለውጥ በእርግጥም ዴሞክራሲያዊ መሆኑን ማረጋገጥ እንችላለን ወይ የሚለው የመጠራጠር ጥያቄ ነው፡፡ ይህም ጥያቄ ቢሆን ካለው አማራጭ ጋር ተዛምዶ ነው መመለስ የሚችለው፡፡ ይህን መንግስት መለመን ወይንም አባብሎ ማውረድ አይቻልም ካልን፣ ሌላው አማራጭ አደጋ ሊኖረው ይችላል ከሚል ብቻ ከመሞከር የሚያግደን ሊሆን አይችልም፡፡ በርግጥ የተፈራው ነገር እንዳይደርስ፣ ይህም የአመፅ መንገድ እንደ ቀድሞው ዴሞክራሲያዊ ስርአትን ሳያመጣ እንዳይደመደም፣ መደረግ ያለባቸውን ጥንቃቄዎች ሁሉ ማድረግ ይጠበቅብናል፡፡ ማህበረሰቡን ከዴሞክራሲያዊ ስርአት ውጪ ሰላምና መረጋጋት ሊኖረን እንደማይችል ማስተማር፣ በማህበረሰባችን ውስጥ ያሉ የተለያዩ አዲስና ነባር ቅራኔዎች በዴሞክራሲያዊ ስርአት ስር ብቻ፣ ሁሉም አሸናፊ በሚሆንበት መፍትሄ እንደሚፈታ ማስተማርና ሁሉም ዴሞክራሲን የሚሹ፣ የአገራችን ፖለቲካ ይመለከተናል የሚሉ ሀይሎች በሙሉ ይህንን አመለካከት እንዲገዙና ከዚህ ያፈነገጠ፣ ግጭት የሚጋብዝ መፍትሄ እንዳይፈልጉ ከወዲሁ አብሮ በመታገል፣ በመተማመንና በመተሳሰብ እንዲሰሩ መጣር ይጠይቃል፡፡ ይህንን ደግሞ ከልባችን ያለመታከት እንሰራበታለን፡፡ ይህም ሆኖ ግን ይህንን በመፍራት ከትግሉ መሸሽ ወይንም የአሁኑን ባርነት በፀጋ ወደመቀበል አይወስደንም፡፡ ይልቁንም ይህንን በምሬት እየታገሉ፣ ወደፊትም የዚህ አይነቱ ችግር በድጋሚ እንዳይከሰት አብሮ ማሰብንና ማስላትን ነው የሚጋብዘው፡፡ የጥያቄው መሰረት ታሪክ ያውም የተለያዩ አለማትን ታሪክ በመንተራስ ከሆነ፣ ዴሞክራሲያዊ ስርአት በትጥቅ አመፅም፣ በሰላማዊ እንቅስቃሴም የመጣባቸው አገሮችን ታሪክ እናውቃለን፡፡ በሰላማዊ አመፅ የመጣ ለውጥ ወደአምባገነንነት ሲሻገር ያየንባቸው አገሮችም አሉ፣ በአመፅ ለውጥ አምጥተው ሌላ አመፅኛ አምባገነንነት የመሰረቱ አሉ፡፡ እንደ አገሩ ታሪክ፣ እንደ መሪ ድርጅቶቹ ምንነት፣ እንደ መሪ ግለሰቦቹ ባህርይና ብስለት የተለያየ ውጤት ይመጣል፡፡ ይህን ጥያቄ ከሚያነሱ ሰዎች ጋር በጥያቄው እንድምታም ባይሆን ጥያቄው በቀሰቀሰው ፍርሀት ላይ ሙሉ በሙሉ እንስማማለን፡፡ ይህን ፍርሀት ለማስወገድም ይህ የአሁኑ የአመፅ ትግል በአገራን የመጨረሻው የአመፅ ትግል፣ የነመለስንም አገዛዝ የመጨረሻው የአገዛዝ ስርአት ለማድረግ አውቀንና አልመን መንቀሳቀስ እንዳለብን እንቀበላለን፡፡

***ጥያቄ፡ ከዚሁ ሳልወጣ፡ አንተ ያልከውን የመንግስት ምንነት ተቀብለንም ቢሆን፣ በመንግስት በኩል የተጋረጠውን ጋሬጣ ሁሉ ተቋዋቁመን፣ በቀድሞው መንገድ ተጉዘን፣ ሕዝቡን አሰባስበንና አደራጅተን በሰላማዊ አመፅ ለውጥ ለማምጣት እንችላለን፣ ለዚህም ቆርጠን ተነስተናል የሚሉ ሀይሎችን ምን ትላቸዋለህ፡፡***

**ዶ/ር ብርሃኑ** እንዴ፣ እነሱንማ ምን እላቸዋለሁ፣ በርቱበት ከማለት በስተቀር፡፡ በርግጥ ይህን አምናችሁ፣ በእርግጥም በሰላማዊ መንገድ ለመታገል ተዘጋጅታችሁና ታግላችሁ ከጣላችሁልን እሰየው ነው እንጂ፡፡ ያው ከላይ እንዳልኩት የጊዜ ገደብ አስቀምጠው፣ በአጭር ጊዜ ካደረጉትና፣ እውነተኛ ለውጥ እስከሆነ ድረስ የሚያስደስት ነው፡፡ ሌሎቻችንንም ከድካምና ከአበሳ ገላገሉን፡፡ የሁላችንም ባለውለታዎች ነው የሚሆኑት፡፡ ይህን ውጤት ስናይም የኛን ትንተና የተሳሳተ ነበር ለማለት እኛም ምንም አይከብደንም፡፡ የሚያሳዝንና የሚያሳፍር የሚሆነው ይህ የሚሉት መንገድ የትም እንደማይደርስ በልባቸው እያወቁ፣ እንዲያው ዝም ብሎ ከመቀመጥ ፖለቲካ ውስጥ አሉ ለመባል፣ ወይንም አንድ የቀድሞ ወዳጄ እንዳለው ‹የተቃውሞ ፖለቲካን እንደ ኑሮ ዘይቤ› በመውሰድ ለጊዜ ማሳለፊያ የሚያውሉት ከሆነ ነው፡፡ በዚያ መልክ የሚንቀሳቀሱ ካሉ ትግሉን እያገዙ ሳይሆን እየጎዱት ነው ለማለት ያስደፍራል፡፡ ይህ ደግሞ ሌላ የትግል መስመር ያዋጣል የምንለውንም ይመለከታል፡፡ ያስኬዳል ብለን የመረጥነው መንገድ በቶሎ ፍሬ እንዲያፈራ ማድረግ ካልቻልን ወይንም አያፈራም ብለን የምናስብ ከሆነ ይህንንው ግልጽ ማድረግና ከጨዋታው መውጣት፣ የተሻለ ውጤት ለማምጣት ለሚችል መልቀቅ ነው እንጂ ዝም ብሎ ለአመታት ምንም ለውጥ የማያመጣ ፖለቲካ ውስጥ ሆኖ ‹አለሁ ለማለት› ብቻ የሚደረግ ትግል ከሆነ ከመቀጠሉ አልቻልኩም ብሎ ማቆምና ለሚችለው መተው ይሻላል እላለሁ፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ኢታሪካዊ በሆነ መንገድ ‹ሰላማዊ ትግልን እንደ ሀይማኖት ቀኖና በመውሰድ፣ አለያም ምንም ደጋፊና አሳማኝ ትንተና በሌለበት ‹የትጥቅ ትግል በአገራችን የተለመደ ነው፣ ያልሰለጠነ አካሄድ ነው› ይልቅስ ያልተለመደውን እንሞክር› ከሚል ‹አዲስ ነገር ሁሉ የተሻለ ነው› የሚል እራስን የመደለያ ግን ውስጡ ለአምባገነንነት ለመንበርከክ ወይም እጅ ለመስጠት ወይንም የራስን ውጤት አልባ እንቅስቃሴ ለመሸፈን የሚደረግ ሙከራ ከሆነ አሁንም የሚጠቅም አይደለም ብዬ አምናለሁ፡፡ ምክንያቱም የዚህ አይነት አካሄድ ቀስ እያለ መጋለጡ አይቀርም፡፡ ለማንኛውም ግን በዋናነት ማለት የምፈልገው ይህን አካሄድ ከልባቸው አምነው የሚከተሉት ያመንገድ የሚወስዳቸው መንገድ ድረስ መሄዳቸው የምንቃወመው ሊሆን አይገባም፡፡ እንዳልኩት ከልባቸው ከሆነና እኛ ያልታየን ነገር የሚታያቸው ከሆነ እንዲያውም ልንደግፋቸው ነው የሚገባው፡፡ እነሱ ሊያደርጉ በፍፁም ልንፈቅድላቸው የማይገባው ግን እነሱ በዚያ መንገድ ለመሄድ በመምረጣቸው ይህ መንገድ አያዋጣም ብለን የምናምነውን ሰዎች አሳማኝ ምክንያት አቅርበው ከመከራከር ውጪ ያ የመረጡት መንገድ እንደማይሰራ ማስተማር አትችሉም፣ ወይንም ደግሞ እነሱ ሞክረን አልቻልንም ብለው እስከሚተዉት ድረስ ሌላ አይነት ትግል መደረግ የለበትም የሚሉ ከሆነ ነው፡፡ ይህን ካደረጉ አሁንም በትግሉ ላይ ደንቃራ እየሆኑ ነው ማለት ነው፡፡ ይህ ደግሞ በእውነትም ለዴሞክራሲያዊ ስርአት ከቆሙ ያደርጉታል የሚል እምነት የለኝም፡፡

**ጥያቄ፡ በግንቦት 7 ሁለገብ የትግል ስልት (ስትራቴጂ) ውስጥ ሰላማዊና የሆነ ህዝባዊ አመጽ ማደራጀት አንዱ እንደሆነ ትናገራላችሁ ፡፡ በሰላማዊ ትግል የጠበበውን የዲሞክራሲ መድረክ ማስፋት እንችላለን ብለው የሚንቀሳቀሱ ሌሎች የፖለቲካ ድርጅቶችም እዚያው ወያኔ አፍንጫ ሥር ሆነን ህዝቡን በመደራጀት ይህንን ማድረግ እንችላለን እያሉ ስለሆነ በአስችኳይ ለውጥ መየት ከሚጓጓው ህዝባችን ከፍሉ የትኛውን መደገፍ እንዳለበት ለመወሰን ግራ እንደተጋባ ይስተዋላል ፡፡ የናንተን ሰላማዊ ትግል ስትራቴጂ ከሌሎች የሚለየው ምንድነው ?**

**ዶ./ር ብርሃኑ፣** ታምራት ይህ ጥያቄም ትንሽ በጥንቃቄ ካለማየትና አጥብቆ ካለማሰብ የሚመጣ ግራ መጋባት ካልሆነ በስተቀር ብዙ ሊያከራክር የሚገባው አልነበረም፡፡ እኛ የገጠመንን አይነት መሰሪ ስርአት በአንድ አይነት መንገድ ብቻ ነው መታገል የሚቻለው ብሎ አጥብቆ የሚከራከር ከምር ሊወሰድ የሚችል ሰው ያለ አይመስለኝም፡፡ በመጀመሪያ ባላንጣህ ራሱ እኮ በጣም በተለያየ መንገድ ነው የሚታገልህ፡፡ የህዝቡን የትግል መንፈስ ለመግደልና በተለይም የሱ ሀይል ምንም ሊቋዋቋዋሙት የሚቻል እንዳልሆነ በእጁ ስር ባሉት የፕሮፓጋንዳ መሳሪያዎች፣ ‹ተማሩ› በሚባሉ አሽከሮቹ በኩል ወሬ በማስወራትና ‹ምሁራዊ› ትንተና በማሰጠት፣ ከዚያ በታች

ያሉ ሩመር በማስወራት የተካኑ ከሼራተን ባሮች በአልኮል ተሞልተው በከተማው ባሉ መጠጥ ቤቶች እየተዛወሩ ወሬ የማባዛት ስራ ብቻ በተሰጣቸው ደካሞች በኩል በየቀኑ አዳዲስ ወሬዎች ሲፈበርክና ሲያስወራ ነው የሚውል፡፡ ከዚያም ያነሱት በደህንነት በኩል በየትናንሽ መጠጫ ቤቶችና ጫት ቤቶች ተመሳሳይ ስራ የተሰጣቸውና ለዚሁ ገንዘብ የሚከፈላቸው ብዙ ወኪሎች ያሰማራል፡፡ ይዚህን መንግስት አይበገሬነት ‹ዝም ብሎ አርፎና ተስማምቶ መኖር እንደሚሻል› ለመስበክና የታጋዮችን ትጥቅ ለማስፈታት ‹የአገር ሽማግሌዎች› በሚል ስም ሰዎችን እያዘጋጀ በተለይ በተቃዎሚዎች መሀል የአላማ አንድነት እንዳይኖር፣ የአላማ ፅናትን ለማዳከም ምንም ነገር እንኳዋን ባይኖር በማስወራትና እርስ በእርሱ እንዲጠራጠር የማድረግ እኩይ ስራ እንዲሰሩለት ያደርጋል፡፡ ከነዚህም ውጭ በዲፕሎማሲው መስክ የአለምን መንግስታት

ልብ ለማማለልና ለብካይ ስርአቱ ድጋፍ ለማግኘት ሌሎች ‹ሽማግሌ ነን ባዮች› ከማዘጋጀት ጀምሮ የአገሪቱን አንጡራ ሀብት በገፍ በመክፈል ሎቢ የሚያደርጉለትን ፈረንጆችን ቀጥሮ ያሰራል፡፡ በማህበረሰቡ ውስጥ ፍርሀትን ለማስፈን ያለ የሌለ ጉልበቱንም በንፁሀን ሰዎች ላይ በመጠቀም ቋዋሚ የሆነ ‹የሽብርና የፍርሀት ስርአት› ፈጥሮአል፡፡ ዞር ብሎ ደግሞ አገር ሰላም ነው፤ ዴሞክራሲ በሽ በሽ ነው ለማሰኘት ተቃዎሚዎች ፓርላማ ገብተው በአመት ሁለት ጊዜ ለጥቂት ደቂቃዎች ‹እንዲሰድቡት› ይፈቅዳል፡፡ ስለዚህ በአንድ መንገድ ሳይሆን በሁሉም መንገድ ነው በስልጣኑ ለመቆየት የሚታገለው፡፡ ታዲያ ይህንን ስርአት አንድ ወጥ በሆነ መንገድ ብቻ ነው መታገል ያለብን የሚለው አመለካከት ከየት ነው የሚመጣው? ለምንድን ነው ይህንን መንግስት ለመጣል የሚደረገው ትግልም በዚሁ ልክ በሁሉም መልክ፤ ይህንን መንግስት ሊያዳክም የሚችል በእጃችን ያለ ወይንም ቀስ እያለ ልናበለጽግ በምንችላቸው መንገዶች በሙሉ የማንታገለው? ለምንድን ነው አንዱ የትግል አይነት ከሌላው የትግል አይነት ጋር የሚጋጭና የሚጣረስ አድርገን የምንወስደው? ለምንድን ነው በዚህ ትግል ውስጥ በተለያየ መንገድ አስተዋፅኦ ለማድረግ የሚፈልገውን ኢትዮጵያዊ ሀይል ሁሉ ለመጠቀም የማንሞክረው? በየትኛው አገር የትግል ታሪክ ነው አንድ አይነት ትግል ብቻ ውጤት አምጥቶ የሚያውቅ? በእርግጥ እንደ አገሩ ሁኔታ፤ እንደ አካባቢው ሁኔታ፤ እንደአለም ሁኔታ፤ እንደገጠመው የባላንጣ አይነት…ወዘተ ከነኝህ የተለያዩ የትግል አይነቶች ውስጥ አንዱ በአንድ ጊዜ ከሌላው የበለጠ ውጤታማ ሊሆን ይችላል፡፡ ግን ያውጤታማ የሆነውም መንገድ ቢሆን በተወሰነ ደረጃ በሌሎቹ የትግል አይነቶች የታገዘ መሆኑ ለውጤታማነቱ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ይኖረዋል፡፡

አሁን ከዚህ በላይ ባልኩት ላይ ብዙም ክርክር ከሌለ አንተ ወደጠየቅከው ጥያቄ በቀጥታ መግባት እችላለሁ፡፡ ግንቦት ሰባት እራሱን እንደ ድርጅት ከማቆሙ በፊት በመስራች አባሎቹ ዘንድ ከፍተኛ ውይይት ከተካሄደባቸው ጉዳዮች አንዱ ይህ የትግል ስልትን በሚመለከት የተደረገው ነው፡፡ በዋናነት በጥያቄው ውስጥ መመለስ የነበረባቸው ሁለት ጉዳዮች ነበሩ፡ እነኝህም

(1)ዴሞክራሲያዊ ስርአትን ለማምጣት ይህ መንግስት መውደቅ አለበት ወይ የሚለው ነው፡፡ ይህን በሚመለከት ቀደም ብዩ በመለስኩት ጥያቄ ውስጥ እንዳልኩት፤ መልሳችን አወንታዊ ነው፡፡ ማለትም በአንድ መልኩ ወይንም በሌላ አሁን ያለው መንግስት፤ አሁን ባለበት መልኩ እስካለ ድረስ ዴሞክራሲያዊ ስርአት ሊመሰረት አይችልም፡፡ ስለዚህም ወይ ተገፍቶ በሚቀበለው ድርድር ሌላ የመሸጋገሪያ ስርአት መፈጠር አለበት ወይንም ደግሞ በፍፁም ተወግዶ ወደ ምርጫ ሊወስደን የሚችል አዲስ የሽግግር መንግስት መመስረት አለበት የሚል መደምደሚያ ላይ ደረስን፡፡

(2)የሚቀጥለው ጥያቄ፤ ይህ ከሆነ ይህን መንግስት ለመጣልም ሆነ ለማስገደድ አመፅ ያስፈልጋል ማለት ነው ወይ? የሚለው ነው፡፡ ይሕንንም ቢሆን ቀደም ብዬ እንዳልኩት የደረስንበት ትንታኔ፤ በምንም መንገድ ይህ መንግስት በፈቃዱ፤ ወይንም በራሱና በድርጅቱ ላይ ሊከተል የሚችለውን አደጋ በቅጡ ካልተገነዘበ በስተቀር፤ ወይንም መውደቁ አይቀሬ መሆኑን ካልገመተ በስተቀር ዝም ብሎ በፈቃዱ፤ ለኢትዮጵያ ጤና ተመኝቶ በሰላም፤ ወይንም ያለምንም የሀይል ግፊት፤ የምእራባውያን ግፊት ቢኖር እንኳዋን ይለቃል የሚል እምነት የለንም፡፡ እንዲያውም ምእራባውያን ፊታቸውን ቢያዞሩበት እንደዚምባብዌና እንደ ሱዳን ከቻይና ጋር ሆኜ እወጣዋለሁ እንጂ በምንም አይነት በሰላማዊ ግፊት አልለቅም ብሎ ወስኖአል ብለን ነው የምናምነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ምእራባውያን እራሳቸው በኢትዮጵያ ዴሞክራሲ እንዲሰፍን ይፈልጋሉ ብለን እነኩዋን ብናምን በመለስ መንግስት ላይ እውነተኛ ጫናን ለመፍጠር በተቃዋሚዎች በኩል ውጤት ሊያመጣ የሚችል አቅም መኖሩን ካላመዛዘኑ ያን ያክል ከምር አይወስዱትም የሚልም ትንተና ነው ያለን፡፡ ስለዚህም በአመፅ ብቻ ነው ሊወድቅ ወይንም ተገድዶ ዴሞክራሲን ሊቀበል የሚችለው ብለን ከምር አምነናል፡፡

እንግዲህ ይህን ትንተና ከተቀበልክ፤ ማለትም የመጨረሻው ጥግ ድረስ የሚወስድ ትግል መደረግ አለበት ካልክ፤ ከዚያ በመለስ ያሉ ሌሎች ትግሎችን እርግፍ አድርገህ ትተዋለህ ማለት አይደለም፡፡ እንደሁኔታው፤ እንደድርጅትህ አይነትና አደረጃጀት፤ አብረውህ እንደሚታገሉት ሌሎች ተባባሪ ሀይሎች ሁኔታ፤ በህዝቡ ውስጥ እንዳለው ስሜት፤ በመንግስት ውስጥ እንደሚፈጠሩት ክፍተቶች፤ ይህን መንግስት ለማዳከምና ለመጣል ይጠቅማል የምትላቸውን የተለያዩ ስልቶች በሙሉ ትጠቀማለህ፡፡ ሕዝቡን ሰልፍ ለመጥራት ወይንም የስራማቆም አድማ ለማድረግ፤ ወይንም ሕዝቡ፡ የመንግስት ሰራተኛው፤ ወታደሩ እንዲለግም ለማድረግ፤ ሁኔታዎች አመቺ ናቸው፤ በግሌ እንደ ድርጅት ወይንም ከሌሎች ድርጅቶችና ሕዝባዊ ማህበራት ጋር በጋራ በመሆን እችላለሁ ብለህ ስታስብ ይህን ሁሉ ታደርጋለህ፡፡ በራስህ ወይንም ከሌሎች ጋራ በመሆን መጠነ ሰፊ የሆነ የፕሮፓጋንዳ ስራ ትሰራለህ፤ ሕብረተሰቡን የምትደርስበትን መንገድ በሙሉ፤ በተለይ ከዘመናዊ ቴክኖሎጂ ጋር ጠንካራ ትውውቅ ያላቸውን አባሎችህንም ሆነ ደጋፊዎችህን ወይንም የሌላ ድርጅት ወይም ሲቪክ ማህበረሰብ አባላትን፤ ነፃ የሚዲያ ተቋዋማትን ተጠቅመህ ታካሂዳለህ፤ በዲፕሎማሲው መስክም በተለይ ይህ ሁሉም በየበኩሉ የሚያደርገው ትናንሽ እንቅስቃሴ ምንም ጠቃሚ ለውጥ እንደማያመጣ ካየሕ በአገራችን ለዴሞክራሲ የቆሙ ማናቸውም ሀይሎች የሚያደርጉትን እንቅስቃሴ አስተባብረው (በሌላ ጉዳዩች ላይ ያላቸው ልዩነት እንደተጠበቀ ሆኖ) እንዲሰሩና አንተም እንደ ድርጅት የዚህ አይነት ትብብር አካል ሆነህ ባለህ አቅም ትሰራለህ…ወዘተ፡፡ ይህ ነው እንግዲህ ሁለንተናዊ ትግል መደረግ አለበት የሚለው የትግል ስልት አጠቃላይ እንድምታ፡፡ ትግሉም በየደረጃው የሚካሄድ ነው የሚሆነው፡፡ እያንዳንዱ የትግል እንቅስቃሴ የሚጠይቀው የሰው ሀይል፤ የገንዘብ አቅም፤ የድርጅት ጥንካሬ፤ ትግሉ የሚካሄድበት ቦታና ጊዜ፤ ለየቅል ሊሆን ይችላል፡፡ ስለዚህ አንድ ድርጅት አንዱን ትግል መቼና በየት ቦታ ወይንም በምን አይነት የሚለውን የራሱን አቅምና አጠቃላይ ሁኔታዎችን እየለካ የሚያካሂደው እንጂ በሬድዮና በፓል ቶክ ከህዝብ ጋር እየተነጋገረ የሚያደርገው እንደማይሆን መቼም እንስማማለን፡፡ በድጋፍ በኩል ደግሞ እያንዳንዱ ሰው የትኛው ድርጅት ነው እኔ ስለአገሬ ካለኝ አመለካከት ጋር የሚቀራረበው? የትኛው ነው በእርግጥም የሚከተለው የትግል መስመር የበለጠ ውጤት የሚያመጣው? የትኛው ነው በእርግጥ የሚያወራውና የሚሰራው የተቀራረበ? በእርግጥ መሰረት ያለው፤ በደንብ የታሰበበት መስመር ያለውና ለዚህም መስመሩ በፅናት ለመታገል ችሎታው፤ ቆራጥነቱ፤ ራዕዩ ያለው ብሎ መደገፍ ይችላል፡፡ ይህ ደግሞ ተገቢ ነው፡፡ በትግሉ ላይ ያለን ማንኛውንም እውነተኛ ድርጅት መደገፍ ይሻላል ዝም ብሎ ይህ ልዩነት ግራ ያጋባል ብሎ እሱን በምክንያትነት እየተጠቀሙ ከዳር ሆኖ ከመቀመጥና ይህ የውርደት ኑሮ እንዲቀጥል መፍቀድ፡፡

እንግዲህ የለም እያንዳንዱ የፖለቲካ ድርጅት ለብቻው የተሰጠው የትግል ስልት መኖር አለበት፤ አንዱ ከአንዱ ጋር መደባለቅ የለበትም፤ ወይንም አንዱን አይነት ትግል አንዱ ድርጅት ብቻ ያድርግ ብሎ ክርክር ሊኖር አይችልም፡፡ ይልቅስ በውይይት ደረጃ የሚጠቅመው በተለያየ ምክንያት እንደዚህ አይነት የተለያየ የትግል ስልት የሚከተሉ ሀይሎች አላማቸው አንድ ከሆነ ትግላቸውን አስተባብረው ቢያካሂዱት የተሻለ ውጤት ሊያመጡ የሚችሉት፤ ስለዚህ ለምንድን ነው ተባብረው የማይሰሩት; የት ላይ ነው ችግሩ ያለው የሚለውን ማየትና ለዚያም መፍትሄ መፈለግ፤ አልፎም ሁነኛ ማህበራዊ ግፊት መፍጠር የበለጠ ጠቀሜታ ያለው ይመስለኛል፡፡

***ጥያቄ.*** **የትጥቅ ትግል በአገራችን ለረጅም ጊዜ ተሞክሮ በመጨረሻው ያመጣ ውጤት ቢኖር ህዝቡን በቋንቋና በባህል አጥር ከልሎ እርስ በርስ እንዲጋጭ የሚያደርግ ፤ በዘላቂውና በጋራ ጥቅማችን እንዳንተባበር የጥላቻንና የመጠራጠርን ስሜት በመካከላችን በማስፈን ማንንም በማይወክሉ አናሳ ያውም ፀር አገርና ፀረ ህዝብ በሆኑ ግለሰቦች እጅ እንድንወድቅ ያደረገንን ሥርዓት አምጥቶአል ። ይህ ባለበት ሁኔታ ከአሁን በኋላ የሚደረግ የትጥቅ ትግል ባለፉት 18 የወያኔ/ኢህአዴግ አገዛዝ የተከፋፈለውንና የተናጋውን የአብሮ መኖር (አንድነት) ጭራሽ ወደባሰ የርስ በርስ ጦርነት ብሎም**

**(ክፍል ሦሥት በሚቀጥለው እትም ይቀርባል)**

## .የሰራልሽ ቀርቶ.... (ከገጽ 1 የቀጠለ)

ዘጋቢያችን ያናገራቸው የአዲስ አበባ ነዋሪዎች “ገና ከጅምሩ በሃስት ማስረጃና ምስክር ሆን ተብሎ ተደርቶ የቀረበ ክስ መጨረሻው ምን እንደሚሆን ለማወቅ ጠንቋይ መቀለብ ባያስፈልግም የመለስ ዜናዊ ዘረኛ አገዛዝ ከአንደ ሃገሩን ከሚወድ ከቅኔና ከግጥም ሌላ ምንም መሳሪያና ድርጅት ከሌለው አንድ ነጹህ ዜጋ ላይ እንዲህ አስከፊ የሆነ ጥላቻና በቀል የተሞላው ድርጊት ሊፈጽም ይችላል ብለው ያሰቡ ጥቂቶች እንደነበሩና የዘረኛው አገዛዝ ፍርድ ቤት ውሳኔ አጅግ ያስደነገጣቸው እንደሆነ ገልጸዋል።

በፍርድ ቤቱ ደጃፍ በዚህ በፍትህ ስም በተካሄደ አይን ባወጣ የበቅል እርምጃ የተከዙ በርካት የቴዲ ደጋፊወችን በማነጋገር ዘጋቢያችን እንደደረሰበት ቴዲ አፍሮ የታሰረው ወንጀለኛ ሆኖም የተገኘው ሃገሩን ስለሚወድ፣ ወያኔ የናቃትንና የጣላትን አረንጓዴ ቢጫ ቀይ ባንዲራችንን ስለሚወድ፣ ወያኔ የዘር ግጭት ሲሰብክ እርሱ ስለአንደነት ወያኔ ስለጥላቻ ሲሰብክ እሱ ስለፈቅር ወያኔ ሃገራዊ ክህደት ሱፈጽም አርሱ ስለሃገራዊ አርበኛነት በመስተማሩ ብቻ ነው፡፡ አንዲት በፍርደ ቤቱ በራፍ ላይ ቆማ የነበረች የቴዲ አፍሮ ደጋፊበጣም የምታለቅስ ወጣት “እነዚህ አረመኔዎች ዛሬ ቴዲን ቸነከሩት፣ የኢትዮጵያ ትንሳኤ ቴዲን በማሰቃየት ተቀብሮ የሚቀር መስሏቸዋል፡፡ በሚሊዮኖች ስለአንድነት ስለፍቅር ስለባነዲራ የሚዘምሩ ተከታዮችን አፍርቷል። ትንሳኤ የማይኖረው ሞት የሚሞቱት እነዚህ ፈሪሳውያንና በሚኒሊክ ቤተመንግስት የህዝብ ስልጣን ዘርፎ የተቀመጠው ጌታቸው መለስ ዜናዊ ነው።” በማለት ሲቃ እየተናነቃት ሀዘኗን ገልጻለች።

## ወያኔ ያቋቋመው ቡድን... (ከገጽ 1 የቀጠለ)

መግለጫው በማስቀጠልም መለስ ዜናዊ የፈጸመውን ወንጀል የሚያጣራ ገለልተኛ አካላት ይቋቋሙ የሚለውን የአለም አቀፉ ሕብረተሰብ ግፊት ወደጎን አድርጎ በራሱ ካድሬዎች በተሞላ የአጣሪ ኮሚቴ የራሱን ማጣርት አድርጎ ራሱን ንጹህ ከምንም ወንጀል ነጻ ነኝ የሚል ሪፖርት ማውጣቱ የመለስን ማንአለብኝነትና ድፍረት የሚያሳይ ነው ብሎታል፡፡ በተለይ ይህ ሪፖርት በመለው አለም በገለልተኛነቱ ከፍተኛ ክብርና በሚያቀርበው ዘገባ ተአማኝነቱ ጥያቄ ውስጥ የማይገባን የሰብአዊ መብተ ተመልካች ድርጅት የፈጠራ ክስ አቅርቦብኛል በማለት የሌባ አይነደረቅ አይነት ውንጀላ ማቅረቡ ለይሉኝታ ቢስነቱ ለከት የሌለው መሆኑን ያሳያል ብሏል፡፡

የሚገርመው ግን ይላል የግንቦት 7 መግለጫ መለስ ዜናዊ ላይ ተመሳሳይ የዘር ማጥፋትና የጦር ወንጀል ክስ ያቀረቡ የሰብአዊ መብቶች ተመልካቹ ድርጅት (human rights watch) ብቻ ሳይሆን ሌሎች እንደ የአለም ቀይ መስቀል ድርጅት፣ አምንስቲ ኢንተርናሺናል፣ ኒዮርክ ታይምስ ጋዜጣና ሌሎች የተከበሩና የሚፈሩ አለም አቀፍ ድርጅቶች ጭምር ስለሆኑ መለስ ዜናዊ የሰብአዊ መብት ተመልካቹን ሪፖርት የሃሰት ፈጠራ ነው ሲል እነዚህንም ታላለቅ የተከበሩ ድርጅቶች በፈጠራ ክስ ተባበሪ ናቸው ብሎ መወንጀሉ አንደሆነ ሊታወቅ ይገባል ብሏል።

መግለጫው አከታትሎም ይህ የመለስ ዜናዊ ቅጥፈት ከተስፋ መቁረጥ ስሜት የመነጨ የሃገሬውን ህዝብና የአለም አቀፉን ህብረተሰብ ለማደናገር የታለመ ቢምስልም እስከ ከዛሬ የተደረጉት ማለቂያ የሌላቸው ቅጥፈትና ማጭበርበር እንኳን ለአገሩ ዜጋ ከአለም አቀፍ ማህበረሰቡም ያልተሰወረ ስልሆነ ከንቱ መፍጨርጨር ነው ብሎታል። ስለዚህም የአለም አቀፍ ማህበረሰቡ መለስ ዜናዊ በኦጋዴን ንጹሃን ኢትዮጵያዊ ወገኖቻችን ላይ በፈጸመው አሰቃቂ ወንጀል ተከሶ ቅጣቱን የሚያገኝበት ሁኔታ ሊያመቻች ይገባዋል በማለት ጥሪውን በማቅረብ የግንቦት 7 ንቅናቄ መግለጫውን ደምድሟል፡፡